# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 2 ቁጥር 68 ታህሳስ 14 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## < <ኢዜማ የሚያምንበትን የዜግነት ፖለቲካ አስተሳሰብ ለሕዝብ አቅርቦ ከተሸነፈ፣ አሸናፊ ሆኖ ወጥቷል ብዬ ነው የማምነው።> >

ኃይሉ አርአያ (ዶ/ር)



# ቆይታ

## < <ኢዜማየሚያምንበትንየዜግነትፖለቲካአስተሳሰብለሕዝብአቅርቦከተሸነፈ፣ አሸናፊሆኖወጥቷልብዬነውየማምነው፡፡> >

ኃይሉአርአያ (ዶ/ር)

የዛሬው የዜጎች መድረክ የ‹‹ቆይታ›› አምድ እንግዳ አንጋፋው ፖለቲከኛ ኃይሉ አርአያ (ዶ/ር) ናቸው፡፡ ከእሳቸው ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንድታነቡት እንጋብዛለን፡፡ መልካም ንባብ!



*ጊዜዎን ሰውተው ከዜጎች መድረክ ጋር ቆይታ ለማድረግ ፍቃደኛ ስለሆኑ በጣም እናመሰግናለን፡፡*

እድሉን ስለሠጣችሁኝ፤በጣም አመሰግናለሁ ፡፡

*ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በኋላ በፓርቲ ፖለቲካ ንቁ ተሳትፎ ሲያደርጉ እምብዛም አንመለከቶትም፡፡ ምክንያቶ ምን ይሆን?*

በጤና ችግር ምክንያት ነው የፓርቲ ፖለቲካ ተሳትፎዬን ያቆምኩት፡፡ ለጤናዬ ትኩረት መስጠት አለብኝ ብዬ ነው ወደ ኋላ ያልኩት፡፡ ፖለቲካውን ግን መከታተል አላቆምኩም፡፡ተመዝግቤና ፎርም ሞልቼ አባል ባልሆንም በመንፈስ ግን ከኢዜማ ጋር ነኝ፡፡

*ኢዜማ የዜግነት ፖለቲካ አዋጭ መንገድ ነው ይላል፡፡ በሌላ በኩል የጎሳ ፖለቲካ በተንሰራፋበት ሀገር የዜግነት ፖለቲካ ብሎ ተነስቶ ሕዝብን ከጎን ለማሰለፍ መሞከር ዘመኑን ያልዋጀ እሳቤ ነው ብለው ትችት የሚያቀርቡ ቡድኖች አሉ፡፡ እርስዎ ይህን መሰሉን አስተያየት እንዴት ይመለከቱታል?*

በእኔ አመለካከት ለዚህች ሀገር የጎሳ ፖለቲካ አያስፈልጋትም፡፡ ዘመኑን ያልዋጀ ብለው ትችት የሚያቀርቡት ቡድኖችም የመርህ ወይም የአቋም ጉዳይ አይደለም ይህንን እንዲሉ የሚያደርጋቸው፡፡ የኢትዮጵያ ህልውና ሊጠበቅ የሚችለው በጎሳ ፖለቲካ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ህልውና ሊጠበቅ የሚችለው በዜግነት መርህ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ ማራመድ የተቻለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ኢትዮጵያን፤ ደህንነቷና አንድነቷን ጠብቆ ከድህነትና ኋላቀርነት ማላቀቅ የሚቻለውም የዜግነት ፖለቲካ በማራመድ ነው፡፡ አዋጩ መንገድ የዜግነት ፖለቲካ ነው፤ አሁን ላይ ግን የዜግነት ፖለቲካን ማራመድ አያዋጣም፤ ስለዚህ ይህንን እምነታችንን ወደ ጎን እናድርገው የሚባል ነገር አይጥመኝም፡፡ኢዜማ የሚያምንበትን የዜግነት ፖለቲካ አስተሳሰብ ለሕዝብ አቅርቦ ከተሸነፈ፣አሸናፊ ሆኖ ወጥቷል ብዬ ነው የማምነው፡፡ እርግጥ ነው፤ ስልጣን አይረከብ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ነገ ላይ ሕዝቡ አማራጩን አይቶ፣ሀሳቡን በደንብ ሲረዳ ኢዜማ አሸናፊ ሆኖ የሚወጣበት እድል ይፈጠራል፡፡

*ኢዜማ የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ትርፍን ብቻ ታሳቢ በማድረግ ከመንቀሳቀስ ይልቅ የረዥም ጊዜ ትርፍን ታሳቢ አድርጎ መንቀሳቀስ አለበት እያሉኝ ነው?*

**‹‹እኔ፣እንደውም ኢዜማ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ምርጫ መወዳደርን ሳይሆን ሕዝብን ማስተማር ላይ ነው መሆን ያለበት ባይ ነኝ፡፡ የሲቪክ ማኅበር አይነት አሠራር በመዘርጋት ሕዝብን የማንቃት ሥራ ቢሰራ የረዥም ጊዜ ትርፍ ማግኘት ይችላል ብዬ ነው የማምነው፡፡››**

አዎ፡፡ እኔ፣እንደውም ኢዜማ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ምርጫ መወዳደርን ሳይሆን ሕዝብን ማስተማር ላይ ነው መሆን ያለበት ባይ ነኝ፡፡ የሲቪክ ማኅበር አይነት አሠራር በመዘርጋት ሕዝብን የማንቃት ሥራ ቢሰራ የረዥም ጊዜ ትርፍ ማግኘት ይችላል ብዬ ነው የማምነው፡፡ኢዜማ፣መጪውን 5 ዓመታት ሕዝብን የማንቃትና የማስተማር ሥራ ቢሰራ ነው የተሻለ ውጤት ማምጣት የሚችለው ብዬ አምናለሁ፡፡ ብዙዎች ይህ ሃሳቤ ላይዋጥላቸው ይችላል፡፡ ሕዝብን የሉዓላዊው ስልጣን ባለቤት ማድረግ የሚቻለው ሕዝብን ወርዶ በማስተማር ነው፡፡ይህንን ለማድረግ ሕዝብን ማብቃት ያስፈልጋል፡፡ ሕዝብ የሉዓላዊው ስልጣን ባለቤት መሆኑን ተረድቶ እንዲንቀሳቀስ የምታደርገው ደግሞ አስተምረህ ያበቃኸው እንደሆነ ነው፡፡ ለዛም ነው ሕዝብን ለማስተማር ትኩረት ሊሰጥ ይገባል የምለው፡፡ ሕዝብ የሉዓላዊው ስልጣን ባለቤት መሆኑን ተረድቶ የሚንቀሳቀሰውም የበቃና የተማረ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

*የጎሳ ፖለቲከኞች ከዜግነት ፖለቲከኞች ይልቅ ድምጻቸው ጎልቶ ይሰማል፡፡ በዛው ልክም ደጋፊዎች አሏቸው፡፡ ደጋፊዎችን ሊያፈሩ የቻሉበት ምክንያትስ ምንድነው ይላሉ?*

ሀገር የሚገነባው በስሜትና በደም በሚመጣ አስተሳሰብ አይደለም፡፡ ደጋፊ አፈሩ ማለት ትክክለኛ ሃሳብ ይዘዋል ማለት አይደለም፡፡ ሕዝብ ያሉት አማራጮች በትክክል ቀርበውለታል ወይ?ጥበብ በተሞላበትና ግልፅ በሆነ መንገድ ያሉት አማራጮች ለሕዝብ መች ቀርበዋል?ተራው ሕዝብ ፖለቲከኛ አይደለም፡፡ ተራው ሕዝብ (የፖለቲካው ንቃተ ህሊናው እምብዛም የሆነው)የጎሳ ፖለቲካን እደግፋለሁ ሲል አልሰማሁም፡፡ ተራው ሕዝብ፣የጎሳ ፖለቲካን ነው የምፈልገው ብሏል ብንል ለዚህ ምን ማሳያ ልናቀርብ እንችላለን?!

*የጎሳ ፖለቲካ ሕዝቡ ዘንድ አልሰረፀም እያሉኝ ነው?*

አስተሳሰቡ የሰረፀው በእኛ (ፖለቲከኞች)ስንፍና የተነሳ ነው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የማስተማር አቅምና ጥበብ ስላጡ እንዲሁም ሕዝብ ዘንድ ወርደው ባለመንቀሳቀሳቸው የተነሳ ነው፤የጎሣ ፖለቲካ ሕዝብ ጋር ሊሰርፅ የቻለው፡፡ ለመስረጹ ኃላፊነት መውሰድ ያለብን እኛው (ፖለቲከኞች) ነን፡፡

*ባሳለፍነው የ2012 ዓ.ም‹‹ኢትዮጵያ እና 5ቱ ሕልመኞች››በሚል ርዕስ አንድ መጽሐፍ አሳትመዋል፡፡በዚህ መጽሐፎ ላይ የለውጡ አመራር ከሚጠብቀው ዋነኛ ፈተናዎች መሀል የጎሳ ፖለቲካን ማስወገድ አንዱ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የለውጡ አመራር የጎሳ ፖለቲካን የማስወገድ ፍላጎት አለው ብለው ያምናሉ?*

ብልፅግና፣ በኢትዮጵያ ምድር

## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ታህሳስ 14 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

መሰረታዊ ችግር የሆነውን የጎሳ ፖለቲካ አልነካውም፡፡ የጎሳ ፖለቲካን የማያስወግድ ከሆነም የጎሳ ፖለቲካ ፓርቲዎች ስብስብ ሆኖ ነው የሚቀረው፡፡ ይህ ደግሞ ለሀገሪቱም የሚበጃት አይሆንም ፡፡ ብልፅግና ወደ ዜግነት አስተሳሰብ የማይመጣ ከሆነ እንደቀደመው ኢሕአዴግ ይሆናል ማለት ነው፡፡ለራሱም (ለብልፅግና) መሠረታዊ ችግር ነው የሚሆነው፡፡ተስፋ የማደርገው የዜግነት ፖለቲካ አስተሳሰብ በሂደት አሸንፎ ይወጣል ብዬ ነው፡፡

*የጎሳ ፖለቲካ አራማጆች ብልፅግና ውስጥ የበላይነት አልያዙም ብለው አያምኑም? እነዚህ የጎሳ ፖለቲከኞች ለጠቅላይ ሚኒስትሩስ ፈተና አይሆኑም?*

በመጽሐፌ እንዳስቀመጥኩት የዜግነት ፖለቲካው አስተሳሰብ የጎሳ ፖለቲካውን አሸንፎ ይወጣል የሚል እምነት ነው ያለኝ፡፡ ይህ ማለት ግን ላይ ላዩን የዜግነት ፖለቲካ አራማጅ በመምሰል ውስጥ ውስጡን የጎሳ ፖለቲካ የሚያራምዱ ከሆኑ ግን እጅግ አደገኛ ነው፡፡

*የለውጡ አመራር ላይ ተስፋ የሰነቁ ይመስላሉ፡፡ በመጽሐፎት ላይም ይህ ይነበባል፡፡ የለውጡ አመራር ወይም በእርሶ ቃል‹‹አዲሶቹየበረሀ ሕልመኞች››ነፃ ምርጫ ቢካሄድ የምርጫ ውጤቱ እነሱ እንዳሰቡት ካልሆነ ውጤቱን የሚቀበሉ ይመስሎታል?*

ገዢው ፓርቲ የሚፈልገው የምርጫ ውጤት ካላገኘ ምርጫውን ተሸንፏል ማለት ነው፡፡ ምርጫውን ተሸንፏል ማለት ደግሞ ሕዝብ አልፈለገውም ማለት ነው፡፡ ሕዝብ አልፈልግህም እያለው ልቀጥል ካለ ደግሞ በጉልበት ብቻ ነው የሚቀጥለው ማለት ነው፡ ፡ ይህ ደግሞ ለራሱ ለገዢው ፓርቲም በጣም አደገኛ ነው የሚሆነው፡፡ስለዚህም ውጤቱን መቀበሉ ለራሳቸውም ነው የሚጠቅመው ፡ ፡ በጉልበት እሄዳለሁ ማለት የተለመደው አዙሪት ውስጥ ነው የሚከተው፡፡

*ታሪክ በተደጋጋሚ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የምንገነባበትን እድል ሲሰጠን ሳንጠቀመው ቀርተናል፡፡ ይህን እድል ካመከንን ከዚህ በኋላ ሌላ እድል የምናገኝ ይመስሎታል?*

ትንቢት ቢኖር እናውቃለን ብለን እንናገር ነበር፡፡ ነገ ምን እንደሚሆን አናውቅም፡፡ ይህ ዓይነቱ ችግር እንዳይከሰት ከፈለግን ሕዝብን በማስተማር ጠንካራ

‹‹ ብልፅግና ወደ ዜግነት አስተሳሰብ የማይመጣ ከሆነ እንደቀደመው ኢሕአዴግ ይሆናል ማለት ነው፡፡ለራሱም (ለብልፅግና) መሠረታዊ ችግር ነው የሚሆነው፡፡ተስፋ የማደርገው የዜግነት ፖለቲካ አስተሳሰብ በሂደት አሸንፎ ይወጣል ብዬ ነው፡፡››

የሆነ የሕዝብ መሰረት እንዲኖር ማድረግ አለብን፡፡የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሕዝብ ጋር አይደለም፤ፖለቲካ እየሰሩ ያሉት፡፡ ሕዝቡን በማስተማር ኃይል እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡ ሕዝብ በራሱ ጉዳይ ላይ አዛዥ እንዲሆን ማንቃትና ማብቃት ያስፈልጋል፡፡ ሕዝቡን አለማብቃታችን ነው፤ ትልቅ ችግር ውስጥ የከተተን፡፡ ታሪክ የሰጠንን እድል ላለማበላሸት ሕዝብ የሚፈልገውን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ሕዝቡ የሚፈልገውን ማወቅ የሚቻለው ደግሞ ሕዝብን የቀረብነው እንደሆነና ፖለቲካን ከሕዝብ ጋር የሠራን እንደሆነ ነው፡፡ታሪክ የሰጠንን ይህን እድል ላለማምከን ሕዝብ የሚፈልገውን ማወቅ ይገባል፡፡

*በያዝነው ዓመት ይካሄዳል ተብሎ የሚጠበቀውን 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ሕገ መንግሥቱ ሳይሻሻል ማካሄድ ፋይዳቢስ ነው፤በተሻሻለ ሕገመንግሥት ነው ምርጫ ማካሄድ ያለብን የሚሉ አሉ፡፡ እርስዎም በመጽሐፎ የሕገመንግሥት ማሻሻያ እንደሚያስፈልግ ገልጸው መሻሻል አለባቸው ያሏቸውን 8 አንቀጾችን ጠቅሰዋል፡፡ከምርጫ በፊት ሕገመንግሥቱ መሻሻል አለበት ወይስ ሳይሻሻል ምርጫው መካሄድ አለበት ነው የሚሉት?*

የሕገመንግሥት ማሻሻያ ይካሄድ ወይስ አይካሄድ በሚለው ነጥብ ላይ በየክልሉ ሕዝበ ውሣኔ ማካሄድ አልያም ደግሞ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሕዝበ ውሣኔ በማካሄድ የሕገመንግሥት ማሻሻያ ያስፈልጋል ወይም አያስፈልግም በሚለው ጉዳይ ላይ ሕዝብ ውሣኔ እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል፡፡ አዲስ ሕገመንግሥት መጻፍም ሌላኛው አማራጭ ነው፡፡ አዲስ ሕገመንግሥት ከማርቀቅ ይልቅ ግን ማሻሻሉ የሚሻለው አማራጭ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ሕገመንግሥቱን የማሻሻሉን ሥራ በስልጣን ላይ የሚገኘው ገዢው ፓርቲም ሊሠራው ይችላል ባይ ነኝ፡፡አሁን ለምርጫ ከመቃረባችን አንጻር ሕገመንግሥቱን ማሻሻል ባንችል እንኳን አሁን በሥራ ላይ ያለውን ሕገመንግሥት ይዘን ምርጫውን ብናካሄድ፣ ምርጫው ፋይዳ ቢስ ይሆናል ብዬ አላምንም፡ ፡

*ለነበረን ቆይታ በጣም ነው የማመሰግነው፡፡*

እኔም፣ አመሰግናለሁ፡፡





# ኢዜማ፣ በውጪ ግንኙነትና ዓለም አቀፍ ትብብር ፖሊሲ፣ በትምህርት ፖሊሲ፣ በባህልና ወጣቶች ፖሊሲዎች ላይ ውይይት አደረገ

ታኅሣሥ 14 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)





የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ቅዳሜ ታኅሣሥ 10 ቀን 2013 ዓ.ም እና እሁድ ታኅሣሥ 11 ቀን 2013 ዓ.ም በዋና ጽህፈት ቤቱ በመስፍን ወልደ ማሪያም አዳራሽ የፖሊሲ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

በሁለቱ ቀናት በተካሄደው አውደ ጥናት ላይ 4 ያህል ፖሊሲዎች ለውይይት ቀርበዋል፡፡ ቅዳሜ ታኅሣሥ 10 ቀን 2013 ዓ.ም በተካሄደው አውደ ጥናት ላይ የውጪ ግንኙነትና ዓለም አቀፍ ትብብር ፖሊሲ እና የትምህርት ፖሊሲ ለውይይት የቀረቡ ሲሆን፣ እሁድ ታኅሣሥ 11 ቀን 2013 ዓ.ም የባህል ፖሊሲና የወጣቶች ፖሊሲ ለውይይት ቀርበዋል፡፡ በአውደ ጥናቶቹ ላይ የፓርቲው ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላቶችና በፖሊሲ ዝግጅቱ ላይ ሚና የነበራቸው ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

የኢዜማ የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪ የሆኑት አማን ይኹን ረዳ፣ ፓርቲያቸው ያዘጋጀው የውጪ ግንኙነትና ዓለም አቀፍ ትብብር ፖሊሲ ኢትዮጵያ፣ አህጉር አቀፍም ሆነ ዓለም አቀፍ ሚናዋን በአግባቡ ለመወጣት፣ ክብሯንም ጥቅሟንም አስከብራ የነቃ ዓለም አቀፍ ተሳትፎ ለማድረግ እንዴት መንቀሳቀስ አለባት የሚለውን የሚመልስ የፖሊሲ ሰነድ መሆኑን ለዜጎች መድረክ ተናግረዋል፡፡ ‹‹አሁን ያለው የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ ብዙ ድክመቶች ክፍተቶች አሉበት›› ያሉት የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪው የዲፕሎማሲው ዘርፍ እውቀት፣ ልምድና ክህሎት የሚጠይቅ ሙያ መሆኑ ተረስቷል ብለዋል፡፡ ‹‹የብሔር ተዋፅኦ መመጣጠን አለበት ተብሎ እውቀትና ሙያተኝነት ተዘንግቷል›› ሲሉም የገዢውን ፓርቲ አሰራር ተችተዋል፡፡

ፓርቲያቸው ኢዜማ በውጪ ግንኙነት ሥራ ላይ የሚሰማሩ ዲፕሎማቶችን በማሰልጠን የሀገራቸውን ጥቅም ማስከበር የሚችሉ፣ ሀገራዊ አርበኝነትን የተላበሱ፣ በዲፕሎማሲ ዘርፍ ውጤታማ የሚያደርጋቸውን የቋንቋ፣ የፕሮቶኮልና ሌሎችም አስፈላጊ እውቀቶች ይዘው ሥራቸውን በአግባቡ መወጣት የሚችሉ ዜጎችን ማውጣት እንደሚችልም ተናግረዋል ፡፡

‹‹ሁሉም ፖሊሲዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲተገበሩና ሀገራዊ ትልሞች እንዲሳኩ ስኬታማ ሥራ በትምህርት ዘርፍ መሰራት አለበት›› ያሉት የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪው አማን ይኹን ረዳ፣ የገዢው ፓርቲ የትምህርት ፖሊሲ ከፍተኛ ችግር ያለበትና ትውልድን የሚገድል ፖሊሲ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ‹‹ሰርተፍኬታቸው የብቃታቸው ማረጋገጫ ያልሆኑ ዜጎችን እንመለከታለን›› በማለት የትምህርት ፖሊሲውን ክሽፈት ኮንነዋል፡፡ ይህም መስተካከል እንዳለበትና ሠርተፍኬት ተሸክመው ወደ ገበያ የገቡትን ዜጎች ማብቃት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡ ፡ ‹‹ብቃት ስለሌላችሁ አታስፈልጉም አይባልም፡፡ ብቃታቸውን ማሻሻል የሚያስፈልግ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል›› በማለት በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ አልፈው ያገኙት ሰርተፍኬት ካላቸው እውቀትና ክህሎት ጋር የማይመጣጠኑ ዜጎች እውቀትና ክህሎት ማዳበር እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል፡፡ ይህም በዋናነት የሚያያዘው ከትምህርት ፖሊሲ ጋር እንደሆነ ጠቁመዋል፡ ፡ ‹‹ከሕዝብ ፍላጎት ውጪ በትምህርት ስርዓት ውስጥ የሚጫኑ ነገሮች አሉ›› ያሉት የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪው ፓርቲያቸው ይሄንን ማስተካከል እንደሚፈልግ ተናግረዋል፡፡

ኢዜማ፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ልጆቻቸው ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙና ድህነትን በትምህርት አማካኝነት ከቤተሰብ እንዳይወርሱ ማድረግ ይፈልጋል ብለዋል፡፡ ‹‹ጥራት ያለው ትምህርት ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ለልጆቻቸው ብቻ የሚያቀርቡት ልዩ ጥቅም ሆኗል›› ያሉት አማን ይኹን ረዳ፣ ፓርቲያቸው ይህንን እንደሚቀይርና ለትምህርት ጥራት

ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጥ አበክረው ተናግረዋል፡፡

ከውጪ ግንኙነትና ዓለም አቀፍ ትብብር ፖሊሲና ከትምህርት ፖሊሲ በኋላ የወጣቶች ፖሊሲና የባህል ፖሊሲ ለውይይት ቀርበዋል፡፡ የወጣቶች ፖሊሲ በወጣቶች አማካይነት እንዲቀረፅ የተደረገ ሲሆን፣ ይህንንም ማድረግ ያስፈልገው የወጣቱን ችግር በሚገባ የሚያውቁት የጉዳዩ ባለቤቶች የሆኑት ወጣቶች ስለሆኑ የወጣቶች ፖሊሲ በወጣቶች አማካይነት እንደተቀረፀ በፖሊሲ አውደ ጥናቱ ላይ ተገልጿል፡፡

ወጣቶች በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካውና በማኅበራዊ ጉዳይ ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችል ሀገራዊ ሁኔታ እንደሌለ የተገለፀ ሲሆን፣ ኢዜማ ይህንን ለመቀየር እንደሚሰራ በውይይቱ ላይ ተነስቷል፡፡ ‹‹የሀገራችንን ወጣቶች በነጻነትና በክብር እንዲኖሩ ትርጉም ያለው የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና ማኅበራዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉና በእውቀት እንዲበለፅጉ፣ በክህሎት እንዲዳብሩ በሥነምግባር ታንፀው እንዲያድጉና ከወጣትነታቸው እድሜ በዘለለ በጎልማሳ እድሜያቸው ጥሩ ወረት ይዘው ለራስም ሆነ ለሀገር እንዲጠቅሙ አስቻይ ሀገር ትፈጥራላችሁ ብንባል የምንሰጠውን መልስ በፖሊሲያችን አካተናል›› በማለት ፖሊሲያቸው የወጣቶችን ጥያቄ ያነገበና የሚመልስ መሆኑን የፖሊሲ አስተባባሪው አማን ይኹን ረዳ ለዜጎች መድረክ ተናግረዋል ፡፡

ታኅሣሥ 11 ቀን 2013 ዓ.ም ከወጣቶች ፖሊሲ በተጨማሪ የኢዜማ የባህል ፖሊሲም ለውይይት ቀርቧል፡፡ ‹‹የባህል ፖሊሲያችን የፖሊሲዎቻችን የማዕዘን ድንጋይ ነው›› ያሉት የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪው፣ ‹‹ኢዜማ ሥራ ሕይወቱ፤ ሥንፍና ሞቱ›› የሆነ ትውልድ መገንባት እንደሚፈልግ ጠቁመዋል፡፡ የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪው ‹‹እስኪደክመው የሚሰራ፣ ሳይሰራ መክበርን የሚጠየፍ ትውልድ መገንባት እንፈልጋለን፡፡ ጠንካራ የሥራ ባህል እንዲፈጠር ትልቅ ሥራ መሥራት እንፈልጋለን፡፡ የባህል ፖሊሲያችን ለዚህ ዝርዝር መልስ አለው›› ብለዋል፡፡

ኢዜማ በጌትፋም ሆቴልና በዋና ጽህፈት ቤቱ እስካሁን ድረስ 12 ፖሊሲዎችን ለውይይት ያቀረበ ሲሆን በቀጣይ ሳምንታትም ሌሎች ፖሊሲዎቹን ለውይይት እያቀረበ የሚቀጥል መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

# የእጩ ምልመላና ድጋፍ ኮሚቴ ምርጫ ወረዳዎች እጩዎቻቸውን የሚልኩበትን ቀነ ገደብ አስቀመጠ

ታኅሣሥ 14 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) እጩ ምልመላና ድጋፍ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት ኢዮብ መሳፍንት፣ ምርጫ ወረዳዎች ኢዜማን ወክለው በምርጫ የሚወዳደሩ እጩዎችን በየወረዳቸው ላሉ የአስመራጭ ኮሚቴዎች በማቅረብ በወረዳቸው ጠቅላላ ጉባኤ እጩዎቻቸውን እስከ ጥር 9 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ማስመረጥ እንዳለባቸው ተናገሩ፡፡

የእጩ ምልመላና ድጋፍ ኮሚቴ በየምርጫ ወረዳዎች አስመራጭ ኮሚቴዎች እንዲዋቀሩ በማድረግ ኢዜማን ወክለው በምርጫ የሚወዳደሩ ሰዎችን ለምርጫ እጩ አድርጎ ለማቅረብ ሲሰራ መቆየቱን ያስታወሱት የኮሚቴው ሰብሳቢ፣ኮሚቴው እስካስቀመጠው የጊዜ ገደብ ድረስ ኢዜማን ወክዬ በምርጫው ለመወዳደር እፈልጋለሁ፣ብቃቱና ኮሚቴው ያወጣቸውን መስፈርቶች አሟላለው የሚል ማንኛውም ዜጋ በምርጫ ወረዳው ላለ የአስመራጭ ኮሚቴ አስፈላጊውን ሰነዶች በማስገባት ራሱን ለውድድር ማቅረብ እንደሚችል ተናግረዋል፡፡ የየምርጫ ወረዳው አስመራጭ ኮሚቴዎች መስፈርቱን የሚያሟላ ተወዳዳሪን ለየ ምርጫ ወረዳው ጠቅላላ ጉባኤካ ቀረቡ በኋላ በወረዳው ጠቅላላ ጉባኤ አብላጫ ድምፅ አግኝቶ ያለፈው ሰው ኢዜማን ወክሎ በምርጫ ወረዳው ለምርጫ እንደሚወዳደር የኮሚቴው ሰብሳቢ ኢዮብ መሳፍንት አስረድተዋል፡፡ሁሉም የምርጫ ወረዳዎች ግን እስከ ጥር 9 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ እጩዎቻቸውን በወረዳቸው ጠቅላላ ጉባኤ ማስመረጥ እንዳለባቸው በአፅንኦት ተናግረዋል፡፡



ምርጫው ግንቦት መጨረሻ ወይም ሰኔ መጀመሪያ ይካሄዳል ተብሎ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መገለፁን ያስታወሱት የኮሚቴው ሰብሳቢ፣ ቦርዱ ቁርጥ ቀን ይፋ ባለማድረጉ ለሥራቸው ከፍተኛ ተግዳሮት እንደሆነባቸው ገልፀዋል፡፡ ‹‹ሌሎች ፓርቲዎች እጩዎቻቸውን ከማዕከል ስለሆነ የሚሰይሙት ትክክለኛ የጊዜ ሰሌዳው አለመገለፁ ብዙም ላይጎዳቸው ይችላል፡፡ እኛ ግን እጩዎችን ከማዕከል ሳይሆን ከየምርጫ ወረዳዎች በምርጫ ወረዳው አማካኝነት የሚመረጡ ስለሆነ ምርጫው የሚካሄድበት ትክክለኛ ቀን እስካሁን አለመገለፁ ለሥራችን እንቅፋት ሆኖብናል››ሲሉ ለዜጎች መድረክ ተናግረዋል፡፡ ቦርዱ በአፋጣኝ ምርጫው የሚካሄድበትን ቀን ይፋ እንዲያደርግም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የእጩ ድጋፍና ምልመላ ኮሚቴ በ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ኢዜማን ወክለው የሚወዳደሩ እጩዎችን በመለየት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሚያቀርብ በምርጫና ስትራቴጂ ማኔጅመንት ኮሚቴ ሥር ካሉ 7 ዘርፎች መሀል አንዱ ነው፡፡





# የኢዜማ የአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 20 እና 23 ውይይት አደረጉ

## ‹‹እንደ ወረዳ መፍትሔ መስጠት ይከብዳል፡፡ ነገር ግን ችግሩ እየከፋ እንዳይሄድ ኅብረተሰቡ የሚደረጉትን ተግባራት ንቁ ሆኖ መመልከት ይገባዋል፡፡››

## ደጀኑ በቀለ (የወረዳ 20 ሊቀመንበር)

ታኅሣሥ 14ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)የአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 23 እና 20 አባላትና አመራሮች እሁድ ታኅሣሥ 11 ቀን 2013 ዓ.ም ውይይት አደረጉ ፡፡

የኢዜማ ምርጫ ወረዳ 23 ለወደፊት የሚመራበት እና ምርጫውን ለማከናወን የሚሰራበትን እቅድ በማዘጋጀት ከአባላቱ ጋር መወያየቱን ለዜጎች መድረክ የገለፁት የምርጫ ወረዳው ሊቀመንበር እንግዳእሸት ገብረማርያም፣ የተጓደሉ አመራሮችን እና ሥራ አስፈጻሚዎችን በአዲስ መተካታቸውን፣ እጩ ተመራጮችና ሥራ አስፈጻሚውም በጋራ እንዲሰራ ምርጫ ወረዳቸው መወሰኑን አስረድተዋል፡፡

በተያያዘ ዜና የኢዜማ ምርጫ ወረዳ 20 ታኅሣስ 11 ቀን 2013 ዓ.ም ባደረገው ውይይት በወረዳው ያሉ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት በቀጣይም በሰበሰቡት መረጃ መሠረት ነዋሪውን ለማናገር እቅድ መያዛቸውን የወረዳው ሊቀመንበር ደጀኑ በቀለ ለዜጎች መድረክ ገልፀዋል፡፡

ወረዳ 20 ላይ የተመደቡ የወረዳው ሠራተኞች እና አመራሮች በሕብረተሰቡ የማይታወቁ፣ የከተማውን የሥራ ቋንቋ መናገር የማይችሉ፣ የነዋሪነት መታወቂያ ለሚያወጣ ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መታወቂያው ምንም አይነት ማሻሻያ ሳይደረግበት 150 ብር ማስከፈል መጀመራቸው፣ በመታወቂያው ላይ ራሳቸው ስህተት ፈጥረው ድጋሚ ለመስጠት 80 ብር እንደሚያስከፍሉ፣ በልማት ሥራ ቤት የፈረሰባቸው ባላቸው ውስን ቦታ ላይ ቤት እንዳይሰሩ እንደሚደረጉና የመሥሪያ ፍቃድ ለማግኘት እጅ መንሻ መስጠት እንደሚጠበቅባቸው፣ በጥቃቅንና አነስተኛ የተሰሩ ሱቆች ለደጋፊዎች ብቻ እየተሰጠ እንደሚገኝ፣ ሕብረተሰቡ ራሱ በመቆጠብ ያቋቋመው የሸማቾች ማኅበር መንግሥት በቸገረው ጊዜ ገንዘብ ያለው ዬታቸው እንደሚወስድ፣ በወረዳው ውስጥ የጸጥታ ችግር በመኖሩ ሕብረተሰቡ አካባቢውን በመፍራት ቤት እንደማይከራይ፣ በዚህ የተነሳም ቤት በማከራየት የሚተዳደሩ ነዋሪዎች መጎዳታቸውን፣ የእድር ማኅበራት ተቀምተው ሥራውን የቀበሌ ተመራጮች ገብተው እንዲያስተዳድሩ በመደረጉ እድሮች ላይ እክል መፍጠሩ የወረዳው ዋና ዋና ችግሮች ናቸው በሚል በውይይቱ ወቅት መነሳቱን የምርጫ ወረዳው ሊቀመንበር አስረድተዋል፡፡

ለእነዚህ ችግሮች በምን መልኩ ነው መፍትሔ ለመስጠት ያቀዳችሁት ብላ ዜጎች መድረክ ላነሳችው ጥያቄ ‹‹እንደ ወረዳ መፍትሔ መስጠት ይከብዳል፡፡ ነገር ግን ችግሩ እየከፋ እንዳይሄድ ሕብረተሰቡ የሚደረጉትን ተግባራት ንቁ ሆኖ መመልከት ይገባዋል፡፡ ይሄ ሥርዓት እንደበፊቱ ሥርዓት በተለመደው መልኩ እንዳይሄድ ስጋት አለብኝ፡፡›› በማለት ምላሽ ሠጥተዋል፡፡

# ኢዜማ‹‹ነገ የምናስባት ኢትዮጵያ በወጣቶች እይታ›› የሚል የወጣቶች የውይይት መድረክ አዘጋጀ

### ያሬድ አለማየሁ (የኢዜማ የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ 23)

ታኅሣሥ 14ቀን 2013ዓ.ም (የዜናች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)ለሁለተኛ ጊዜ ነጻ የወጣቶች የውይይት መድረክ ታኅሣሥ 15 ቀን 2013 ዓ.ም ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ጀምሮ በመስፍን ወልደ ማርያም አዳራሽ እንዳዘጋጀ የኢዜማ ወጣቶች ጉዳይ ተጠሪ ያሬድ አለማየሁ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

በኢዜማ ወጣቶች ጉዳይ በኩል የወጣቶች የውይይት መድረክ ከዚህ በፊት አንድ ጊዜ የተደረገ መሆኑን ያስታወሱት የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪው፣ሐሙስ ታኅሣሥ 15 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የውይይት መድረኩ በየወሩ አጋማሽ ሳይቋረጥ እንደሚቀጥልና የኢዜማ አባላት ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ወጣት በውይይት መድረኩ ላይ መሳተፍ እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

‹‹የኔ ፖለቲካ››በሚል በየወሩ የሚዘጋጀው ዝግጅት ወጣቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸው ስጋቶቻቸው፣ተስፋዎቻችው፣የወጣቶች ሚና እና ተግዳሮቶች ላይ ትኩረት የሚያደርግ የውይይት መድረክ ነው፡፡

‹‹ነገ የምናስባት ኢትዮጵያ በወጣቶች እይታ›› በሚል መሪ ቃል ሐሙስ ታኅሣሥ 15 ቀን 2013 ዓ.ም በሚደረገው ውይይት ወጣቶች የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ለምንድን ነው ያልተሳተፉት?ፖለቲካውን የሚርቁት ከምን የመነጨ ነው?በሚል ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ውይይት የሚደረግ ሲሆን፣ የመወያያው መድረክ ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት የፖለቲካ ተሳትፎ ለሌላቸው ወጣቶች ታስቦ የተዘጋጀ እንደሆነ ተጠሪው ጠቁመዋል፡፡

ከውይይቱ በተጨማሪ በወጣቱ ዘንድ የውይይት ባህል ለማዳበር፣ አዳዲስ አባላትን ለመመልመል፣ ደጋፊዎችን ለማፍራት እንዲሁም ባላቸው ሙያ ኢዜማን እንዲያግዙ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ እንደሚገኝ የኢዜማ የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪው ያሬድ ዓለማየሁ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡



‹‹ወጣቶች ተመሪ ብቻ ሆነው ወደ ጥፋት እንዳይሄዱ ቆም ብለው ማሰብ ይገባቸዋል፡፡ወጣቶች መሪ መሆን፣ትልቅ ደረጃ መድረስ የሚችሉ መሆናቸውን አስበው፣ለንግግር ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፡፡ በያዝነው ዓመት በሚካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይም ወጣቶች በንቃት መሳተፍ ይገባቸዋል››በማለት ወጣቶች ሚናቸውን ተረድተው በኃላፊነት መንቀሳቀስ ከቻሉ መሪ መሆን የሚችሉ የነገ ሀገር ተረካቢዎች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

# ‹‹ባህርዳር የክልሉ መቀመጫ ከመሆኗ አንጻር ከማዕከል ትኩረት ሊሰጥ ይገባል››

### መንግሥቱ አማረ (የኢዜማ የባህር ዳር ምርጫ ወረዳ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ)

ታኅሣሥ 14ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በባህር ዳር ከተማ ለሥራ አስፈጻሚዎች ሥልጠና መስጠቱን የኢዜማ ባህር ዳር ምርጫ ወረዳ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ መንግሥቱ አማረ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

የምርጫ ዝግጅት እና አደረጃጀት፣ የሕዝብ ግንኙነት ዋና መሠረቶች እና የፓርቲውን አሠራር መሠረት ያደረገ ሥልጠና ለአመራሮች መሰጠቱን ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው አስረድተዋል፡፡ በባህር ዳር በተሰጠው ሥልጠና እና በተደረገው ውይይት በምርጫ ወረዳ ደረጃ 15 ወጣቶችና 15 ሴቶች፣ በክፍለ ከተማ ደግሞ 5 ወጣቶችና 5 ሴቶች የመመልመል ሥራ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ኃላፊው ጠቁመዋል ፡፡ የሕብረተሰቡን ችግሮች የሚለይ፣ የማኅበረሰቡን ጥያቄ ምን እንደሆነ አጥንቶ መፍትሔ የሚያስቀምጥ ቡድን ተቋቁሞ ዘለቄታዊ ሥራ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ አሳውቀዋል፡፡

ኢዜማን ወክሎ በሀገር አቀፍ ምርጫ መወዳደር የሚፈልግ የባህር ዳር ነዋሪ የኢዜማንና የምርጫ ቦርድን መሥፈርት በማሟላት እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ በመመዝገብ በምርጫው ላይ መሳተፍ እንደሚችል ያስረዱት የኢዜማ የባህር ዳር ምርጫ ወረዳ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው መንግሥቱ አማረ፣ ባህር ዳር የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መቀመጫ ከመሆኗ አንጻርም ከማዕከል ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ብለዋል፡፡

## የአቶ ወርቁ ፍጀው ቤተሰቦች ለአባታችን ማስታወሻ እንዲሆን በማለት ለኩታበር የምርጫ ወረዳ የ100,000 ብር እርዳታ አደረጉ።

አቶ ወርቁ ፍጀው፣ ውልደታቸው በወሎ ክፍለ ሀገር ዋድላ ደላንታ ወረዳ ሲሆን አብዛኛውን የልጅነት ህይወታቸውን ያሳለፉት በኩታበር ከተማ ነው። አቶ ወርቁ ፍጀው በተወለዱ በ83 ዓመታቸው ነሐሴ 25 ቀን 2010 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሲሆን፣ ልጆቻቸው አባታችን እንዲታወስ የምንፈልገው ባደገበት ከተማ የሚደረገውን የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ሂደት በማገዝ ነው በሚል አባታቸው ላደጉበት ለኩታበር ከተማ፣ የኢዜማ የዋድላ ደላንታ ምርጫ ወረዳ በአባታቸው ስም የ100,000 ብር እርዳታ ለግሰዋል።





# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ኢዜማ ካስገባው አቤቱታ ይፋዊ ማብራሪያ ሰጠ

## “ኢዜማ ለቦርዱ ደብዳቤ ካስገባ በኋላም በወላይታና ሃድያ ዞን ተመሳሳይ ድርጊቶች እየተደረጉ ነው”

### ዋሲሁን ተስፋዬ (የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ)

ታኅሣሥ 14ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአማራና በደቡብ ክልል የምርጫ አስፈጻሚ አባላት ምልመላ እየተከናወነ በመሆኑ ቦርዱ ማብራሪያ እንዲሰጠው በጠየቀው መሠረት ቦርዱ በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል ምላሽ ሰጠ፡፡

ቦርዱ ምርጫን የማስፈጸም፣የማስተዳደር እና የፓለቲካ ፓርቲዎችን የመመዝገብ እንዲሁም ገለልተኛ እና ብቁ የሆኑ የምርጫ አስፈጻሚዎችን የመመልመል ኃላፊነት የቦርዱ መሆኑን በማሳወቅ እጩ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች ዝርዝር ለማዘጋጀት ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን በማብራሪያው አሳውቋል፡፡

ቦርዱ የተለያዩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ያሏቸውን መረጃ እንዲያጋሩት በጠየቀው መሠረት የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን እና የተለያዩ ተቋማቶች ለተለያዩ ጉዳዮች ያሰባሰቧቸውን መረጃዎች ለቦርዱ ማጋራታቸውን፣ ቦርዱም በራሱ መስፈርቶች ዝርዝሮቹን በማጣራት ሊጠቀምባቸው የሚችልበትን መንገድ እያመቻቸ እንደሚገኝ፣ በማንኛውም የመንግሥት መዋቅር በኩል የምርጫ አስፈጻሚዎችን ምልመላ እያከናወነ እንዳልሆነ፣ከቦርዱ ውጪ ለምርጫ አስፈጻሚነት የሚደረጉ ምዝገባዎች የቦርዱን አሰራር ያልተከተሉ መሆናቸውንና ቦርዱ ክፍተት ካገኘ የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወስድ በማብራሪያው ላይ ገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይሄን ቢልም የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ፣ ቦርዱ ኢዜማ ላቀረበው ጥያቄ በአደባባይ መልስ ከመስጠት ይልቅ በደብዳቤ መልስ ሊሰጠን ይገባ ነበር ብለዋል፡ ፡ ‹‹ለእኛ ሳይመለስ በአደባባይ ነው መልስ ለመስጠት የተሞከረው፤ በደብዳቤ ጠይቀናል በደብዳቤ መልስ ሊሰጠን ይገባል፡፡ አሁንም በደብዳቤ ምላሽ እንጠብቃለን›› በማለት ቦርዱ በማኅበራዊ ሚድያ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በደብዳቤ ጥያቄውን ላቀረበው ኢዜማ ምላሽ ቢሰጥ የተሻለ እንደነበር ጠቁመዋል፡፡ ኢዜማ ለቦርዱ ደብዳቤ ካስገባ በኋላም በወላይታና ሃዲያ ዞን ተመሳሳይ ድርጊቶች እየተደረጉ እንደሚገኝ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡

